# <u>የመለስ ባህሪያትና ኢትዮጵያ</u>

**ራሚደስ 27/12/04**

የቀድሞው ጠቅላይ ሚንስትር መለስ ዜናዊ በህይወት ዘመናቸው የተላበሱት ግለ-ባህሪያት ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ነፍሳቸው ከስጋ ከተላቀቀች ጀምሮ ማወዛገብ የጀመረ ይመስላል:: በአፍቃሪዎቻቸውና በአድናቂዎቻቸው እይታ መለስ ፅናት ያለው ፣ ለህዝብ ተቆርቋሪ ፣ አገር ወዳድ ፣ ምርጥ ዲፕሎማት አድርገው ሲስሏቸው ተቃዋሚዎቻቸውና ላለፉት ሁለት አስርተ አመታት ገደማ የአቶ መለስን አገዛዝ በአንክሮ የተከታተሉ ታዛቢዎች ደግሞ በተቃራኒው ጭካኔያቸውን ፣ አድሎአዊነታቸውን ፣ አምባገነንነታቸውን አልፎ ተርፎም አልሸነፍ ባይነታቸውን ሲያመላክቱን ይታያሉ:: ህይወቱ ከዚች ዓለም ለተሠናበተ እና አስክሬኑ ሰባት ክንድ ከምድር በታች ስለተሸኘ ሰው ግለሰባዊ ባህሪ መተቸቱ አስፈላጊ መስሎ ባይታይም ቅሉ ቢከፋም ቢለማም እንደ መሪ አገሪቷና ሕዝቧ ላይ ያሳረፉት ተፅእኖ ቀላል ባለመሆኑ ፣ ከዚህም በኋላ ለሀገሪቷ እና ሕዝቧ መፃኢ እድል የአቶ መለስ የ21 ዓመት አገዛዝ የማይናቅ አንድምታ እንደሚኖረው በመገመት፣ በተጨማሪም አቶ መለስ ለወደፊቱ ትውልድ ትተውት ያለፉትን የታሪክ አሻራ መዳሰሱ ግድ ስለሚል የሳቸውን ግለ- ባህሪያት አጠር ባለች መልኩ መቃኘቱ አይከፋም::

በመጀመሪያ ደረጃ አቶ መለስ ወዳጅም ጠላትም የሚመሰክርላቸውና የሚታወሱበት ባህሪያቸው **ፅናታቸው** ይመስላል:: ምንም እንኳን በቀድሞ የትግል ጓደኞቻቸው በሜዳው ላይ ፈሪነታቸውን በበርካታ ጊዜያት ቢመሰክርባቸውም ቅሉ በረሃ ገብተው ፣ በድርጅታቸው ከጋንታ ም/ኮሚሳርነት እስከ የአመራር ወኪል ፣ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል ፣ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል ፣ ሊቀመንበርና የሀገር መሪ እስከ መሆን ያሉትን ጠመዝማዛና እጅግ አድካሚ መንገዶች በፅናት ማለፋቸው የማይካድ ሀቅ ነው:: በእንግድነት ከተጋበዙበት ቤት ከማጀት ሳይወጡ ለረጂም ሰዓት በማንበብ መፅናታቸው ሊጥ ለማብካት ያልቻሉት ሴትዮ «አያስቦካ» የሚል ቅጸል ስም እስከ ማውጣት የተደረሰላቸው አቶ መለስ ከትግል ህይወታቸው ባለፈም በ 19 ዓመታቸው አቋርጠው ወደ በረሃ የገቡትን የዩንቨርስቲ ትምህርት በቤተ- መንግስት ዙፋን ከተቀመጡም በኋላ ሳይታክቱ በተቃዋሚው ጎራ በብዛት እንዳሉት «ባለአንጣዎቻቸው» እሳቸውም የዶክትሬት ዲግሪ ካባ መልበሳቸው ተነግሯል:: በአለማችን መሪዎች የእለት ማስታወሻ ከመያዝ ባላለፈ በቀን ተቀን ሀገርንና ህዝብን የማስተዳደር ስራ ላይ ተጠምደው ሳለ አቶ መለስ ከተራ የግለሰብ ደብዳቤ እስከ ጋዜጣና መፅሄት አምደኝነት አልፎ ተርፎም የካድሬ ማሰልጠኛ ማንዋሎችን ፣ የሀገር ፖሊሲዎችንና የዶክትሬት መመረቂያ ጥናት ሲፅፉ እንደከረሙ ለታዘበ ሰው የሰውየውን ፅናት እንደሚረዳ ጥርጥር የለውም::

ሌላው የአቶ መለስ ግለ-ባህሪ **ብልጣብልጥነታቸው** ነው:: አድዋ በሚገኙት የዳኛውና የሰይጣን መዋኛ ተብለው በተለምዶ ከሚታወቁት ሁለት ጅረቶች በልጅነታቸው ከሚያዘወትሩት የውሃ ዋና ቀጥሎ በብይ ጨዋታ መቆመርን ይወዱ እንደነበር «ገድለ-ታሪካቸውን» ከፃፉላቸው የትግል ጓዶቻቸው ለማወቅ ተችሎአል:: የተማሪ ቤት ጓደኞቻቸውም አቶ መለስ በዊንጌት ት/ቤት ተማሪ ሳሉ ከጃንሆይ ይላክላቸው የነበረውን የጎበዝ ተማሪ ማበረታቻ ገንዘብ እንደተቀበሉ ወደ ካርታ ቁማር ይዘው ከተፍ ይሉ እንደነበር መስክረውባቸዋል:: ይህ ቁማር

ጨዋታ ልምድ ምናልባትም ሰውየው ከተላበሱት ብልጠት ባሻገር የሚያጠነጥነው «ለእኔ» የምትለው አባዜ ብልጣ ብልጥ ባህሪ ሳያጎናፅፋቸው አልቀረም:: ለዚህም ይመስላል አቶ መለስ የወያኔ ጉምቱ የተባሉትን ግለሰቦች ከነግደይና አረጋዊ ጀምሮ እስከነ ስዬ ፣ አረጋሽ ፣ ተወልደ ና ሌሎችም «አይነኬዎች» ተራ በተራ ጠልፈው ለመጣል የቻሉት:: እነ ሌንጮ ፣ ታምራት ላይኔ እና ሌሎች በርካታ «የዋሖች» የዚች የብልጣብልጥነት ባህሪ ተጠቂ መሆናቸው አይካድም:: ነጮቹስ ቢሆኑ አቶ መለስን ለማወቅ ያውም የተቃዋሚዎች ያላሰለሰ የማሳበቅ ስራ ተጨምሮበት ከ15 ዓመታት በላይ አልፈጀባቸውም ? አሁንም ቢሆን የአቶ መለስ በግብር ጫና፣ በብድርና እርዳታ፣ ከውጪ በሚመጣ ሪሚታንስ ፣ ገንዘብ በማተም ወዘተ የሚያሳዩትን ብልጭልጭ የኢኮኖሚ እድገት ከአጠቃላይ ሰብኣዊና ማህበራዊ ልማት ጋር እያምታቱ ያሉ ነጮች ቁጥር ቀላል አይደለም::

ሶስተኛው የአቶ መለስ ባህሪ **የተከራካሪነት** አባዜ ነው:: ምናልባትም በእርሳቸው ዘመን በነበረው ስርዓተ-ትምሕርት ክርክር የተለመደ እና የሚዘወተር በመሆኑ ከልጅነታቸው የተቀረፀበት የክርክር መንፈስ በእድገታቸው እና በጉልምስናቸው ብሎም እስከ ህልፈተ-ህይወታቸው ድረስ አብሮአቸው አንደኖረ ይታመናል:: ይህ የተከራካሪነት ልምድ በጥሩ የቋንቋ ክህሎት ጋር ተዳምሮ እየጎለበተ መጥቶ በድርጅታቸው የላይኛው የስልጣን ማማ የመቆናጠጥ ብቻም ሳይሆን በአፍሪካ እና በዓለም ደረጃ ጥሩ ተናጋሪ ፣ ተናግሮም አሳማኝ ፣ የአፍሪካ-አፈቀላጤ ወዘተ የሚል ስም አጎናፅፎላቸዋል:: በአገር ውስጥ አመራራቸው ደግሞ ከሳቸው ሀሳብ ወጪ ሌላ ሊያስተናግዱ ፍፁም ፍቃደኛ ያልነበሩት አቶ መለስ አመክንዮ ላይ የተመረኮዘ ክርክር አንስቶ ሌላኛውን ወገን ግለሰባዊ ማንነት እስከ ማንኳሰስ በሚደርስ መልኩ አሸማቀው ማለፍ የተለመደ ባህሪያቸው መሆኑን የፓርላማ ንግግሮቻቸውን ማስታወሱ በቂ ይመስላል::

በአራተኛ ደረጃ የሚቀመጠው የአቶ መለስ ባህሪ **ጠላፊነታቸው** ነው:: እሳቸው ቀደም ብለው ያላነሱት ሃሳብ በሌላ ሰው ሲነሳ ያንን ሰው ከላይ በገለፅናቸው ባህሪያት ተከራክርውና አሸማቀው ጥግ ካስያዙ በኋላ በተለመደችው የብልጣብልጥነት መንፈስ የሌላውን ሰው ሃሳብ በመጥለፍ በራሳቸው ቅኝነት ቋጥረው እንደ አዲስ ሀሳብ አፍላቂ ብቅ ማለትን ተክነውበታል:: ከንጉሱ ዘመን አንስቶ የነበሩትን የብሔርና የሃይማኖት እኩልነት ጥያቄዎች ከባለቤቶቹ ጠልፈው እንደወራሽ ብቻም ሳይሆን «ካንተ በላይ አውቅልሃለሁ» እስከማለት የሚደርሱ ደፋር መሆናቸውን አሳይተውናል:: ለይስሙላ የጠለፏቸው የመብት ጥያቄዎች እያመረቀዙ መውጣታቸው የብሔር ነፃ አውጪዎች ዳግም መፈልፈል ብቻም ሳይሆን የሃይማኖት መብት ጥያቄዎች በአሁኑ ጊዜ ሀገሪቷን ወጥረው ከያዟት አንኳር ጉዳዮች ውስጥ መሆናቸው የሰውየውን የጠላፊነት ባህሪ ፍንትው አድርገው እያሳዩን ይገኛሉ:: ከገጠር ወደ ከተማ መር ፣ ከእርሻ ወደ ኢንዱስትሪ እንዲሁም ሴቱንና ወጣቱን የመጠርነፍ አካሄድ ከቅንጅት ማኔፌስቶ የተጠለፉ አስተሳሰቦች እንደሆኑም ይታመናል::

ሌላው የአቶ መለስ ግለ-ባህሪ **ንቀት** መሆኑ አይካዴ ነው:: ይህ ንቀታቸው የማን አለብኝነትና የአምባገነንነት አባዜ እንደወለደባቸው አያጠራጥርም:: ቀይ ባህርን ቆርጦ ምን ትሆን ከማለት አንስተው እስከ የሀገርን ታሪክና ሰንደቅ ዓላማን የማንቋሸሽ አባዜ እብደት ካልሆነው ለህዝብ ያላቸው ንቀት ገላጭ መሆኑ ግልፅ ነው:: የተከራካሪናት ባህሪያቸው ጋር

አያይዘን የገለፅነው የተራ ስድብና ግለሰቦችን የማሸማቀቅ አካሄድ ከዚሁ ካዳበሩት የንቀት ባህሪ ጋር የሚዛመድ ይመስላል:: ከ«እጆቻችሁን እንቆርጣለን» እስከ «በሊማሊሞ አቋርጡ» የሚሉት አነጋገሮች የዚሁ የንቀት ባህሪ ምልክቶች ይመስላሉ:: እርግጥ ነው ይህ ንቀታቸው የመነጨው በባዶ ሳይሆን ጀርባቸውን በመተማመናቸው ነው:: «በለማሊሞ አቋርጡ» ከሚሏቸው ነጮች ጋር እንኳን በጓሮ በር መሞዳሞዳቸው አይቀሬ ሆኖ ሳለ «እጅህን እቆርጥልሃለሁ» የተባለው ህዝብ ግን ቃል ቢተነፍስ አስተነፍሳዋለሁ ብለው የተመኩበት ሀይል ከደጀን ቆሞ ስለሚጠብቃቸው ይመስላል ይህን ሁሉ ንቀት ህዝቡ ላለፉት ሁለት አስርተ ዓመታት እንዲያስተናግድ የተገደደው:: ይህ የሚመኩበት ሀይልን ሊያዋቅሩ እና ሊያደራጁ የቻሉት ደግሞ ከዚህ በታች በምናየው ባህሪያቸው ላይ በመንደርደር ይመስላል::

ይህም **የተጠራጣሪነት** ባህሪያቸው ነው:: ከመከላከያና ደህንነት መዋቅሮች ባሻገር የመንግስት መ/ቤቶች፣ የትምህርትና የሃይማኖት ተቋማት ፣ ሲቪክ ማህበራትን ፣ ወጣትና የሴቶች ሊግ፣ ከአነስተኛ እስከ ከፍተኛ ነጋዴዎችን ወዘተ በራሳቸው ሰዎች (የፖለቲካ አመለካከት ሳይሆን ይበልጡኑ በጠባብ የብሔር ማንነት ላይ በተመረኮዘ) ጠርንፈው መያዛቸው የሰውየውን ተጠራጣሪነት ብሎም ፈሪነት ቁልጭ አድርጎ ያሳያል:: ከመንግስት መዋቅር በዘለለ ከራሳቸው ብሔር ውጪ ያሉ «ሌሎች» ባለሐብቶችን እንኳን ሳይቀር የሚጠራጠሩት ሰው ብልጣብልጥነታቸውን ተጠቅመው ከሙስና ጋር በተያያዘ «የጎጃም ኢምፓየር» የሚሉትንና በወፍ ጉንፋን ደግሞ «የጉራጌ ኢምፓየርን» እንዲሁም በወርቅና ላሜራ ትርኢት «የስልጤ ኢምፓየርን» ማፈራረሳቸውን በኩራት እንደሚናገሩ «የውስጥ» ሰዎች ሲያንሿክኩ ተሰምቷል:: እኝህ በጣም ተጠራጣሪ የሆኑ ሰው በከተማው ወ/ሮ ዘርፈሽዋል እየተባሉ የሚወቀሱትን ባለቤታቸውን አይናቸውን በጨው አጥበው ከተራ «ሚስትነት» አንስተው እስከ «ትግራይ ኢምፓየር -ኢፈርት» መሪነትና እስከ ህ.ወ.ሀ.ት ስራ አስፈፃሚ ኮማቴ አባልነት ማሳደጋቸው የዚሁ የተጠራጣሪነት አባዜ ውጤት እንጂ ሌላ አይደለም:: የገዛ ዘመዶቻቸውን የሚጠራጠሩት ሰው የነ አቶ አርከበን አንስቶ መጣል፣ ከአንድ ፕሮፌሰር አራተኛ ክፍልን ያላጠናቀቀ ገበሬ ይሻላል በሚል ብሂል «በእሺ ጌታዬ» ሰዎች መከበባቸውን፣ እስክሪቢቶ ይዘው የተነሱትን ጋዜጠኞች ዘብጥያ ማውረዱ፣ አስቀድሞ ህዝቡ ላይ ፍርሃት እንዲነግስ የማድረግ አባዜ ፣ እንዲሁም ከሀገሪቱ ገጠር ልማት ፖሊሲ እስከ ኢንዱስትሪና የከተማ ልማት አልፎ ተርፎም የውጭ ጉዳይና ደህንነት ፖሊሲዎች በብቸኝነት የማርቀቅ አካሄዳቸው ከመጠን ያለፈ የተጠራጣሪነት መንፈስ እንዳደረባቸው እሙን ማስረጃ ይሆናሉ::

እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት ስድስት ዋና ዋና ግለ-ባህሪያት የሰውየውን የህይወት ጉዞ መቃኘታቸውና ለእስከ ዛሬዋ አስተዳደራቸው የራሳቸውን ጠባሳ አሳርፈው እንዳለፉ ባያጠራጥርም ለመጪው የአገሪቷ መፃኢ እድልም ቀላል የማይባል ተጽእኖ እንደሚፈጥሩ መገመቱ ግድ ይላል::

ሀገሪቱ በጣም ደካማና የህዝብ አመኔታ የሌለው መንግስት እንዳወረሷት ሁሉ የጦርና የደህንነቱ መዋቅር ግን በተቃራኒው ጠንካራና በጥቂት የጎጥ ልጆች የሚታዘዝ አድርገው አዋቅረው ማለፋቸው ከሳቸው በኋላ ለምትኖረው ኢትዮጵያ አሉታዊ ገጸታ እንደሚያላብስ ሳይታለም የተፈታ እውነታ ነው:: ጥቁሩጥቲን ተብለው የወላይታውን የእየሱስ ተከታይ ከፊት አሰልፈው ለማሽከርከር አቅደውት የነበሩት ሃሳብ እነሆ አፈር ከበላው ቀን አንስቶ ሀገሪቱን

በየመስኩና በየደረጃው የሚያሾሯት የትግራይ ልጆች መላ ቅጡ እንደጠፋባቸው ብዙ ይወራል። እንደ ሰውየው በብልጣብልጥነት ተከሽነው እራሳቸው የከተቡትን የአገሪቷን ህገ- መንግስት ሳይጥሱ ለመጓዝ የአቶ ሀይለማርያምን ተጠባባቂ ጠቅላይ ሚንስቴርነት ማፅደቅ ግድ ይላቸው። ዳሩግን ከሰውየው የወረሱት ተጠራጣሪነት ዳግም ይህንን መንገድ አይነኬ እንዲሉ ሳያስገድዳቸው የሚቀር አይመስልም። እንኳን ብሔራዊ እርቅን፣ ለተቃዋሚ ስልጣን የማጋራትንና የፖለቲካ ምህዳሩን የማስፋት ጥያቄዎችን መመለስ ቀርቶ ከዚያው ከኢ.ህ.አ.ዴግ መንደር የወጡ አልፎ ተርፎም ከጀርባቸው እንደ ኦ.ሆ.ዴ.ድ «ጠባብነትና ኦነግ» እንደ ብ.አ.ዴ.ን «ትምክህትና ቤተክህነት» የሚል ልጣፊ የሌለባቸውን ሰው ለማመን ሲያዳግታቸው ይስተዋላል።

የአቶ መለስ ግለ- ባህሪያት ወራሾች መላ ቅጡ በጠፋ ጥርጣሬና ፍርሀት መተብተባቸው ግልጸ ሆኗል። የወላይታው ሰው የብ.አ.ዴ.ን ና የኦ.ሆ.ዴ.ድ እንዲሁም የሌሎች አጋር ድርጅቶች ድጋፍ ቢያገኙስ ? ሰብዓዊ መብትና ዴሞክራሲ እያሉ የሚያላዝኑት የአውሮፓና የአሜሪካ የፕሮቴስታንት እምነት ተከታይ ጎያላኖች አይዞህ አለንልህ ቢሏቸውስ ? በዚህም ተደፋፍረው ማን ያውቃል የመከላከያና የደህንነት ቁልፍ አመራሮችን በአንድ ጀንበር ቢለውጡስ ? ወዘተ በሚሉ ጥርጣሬዎች ቅዠት ከጀመሩ ሰንበትበት ብለዋል ነው የሚባለው።  የአቶ መለስ ቀብር አለ ቅጥ የተራዘመው ለምን ይሆን ? ለለቅሶ ? እድሜ ለማያሳፍረው የኢትዮጵያ ህዝብ አልቃሽ መች ጠፋና። አቶ ሀይለማርያምን ቃለ- መሃላ ለማስገባት ተጠርቶ የነበረውን ፓርላማ ለምን ተላለፈ? ቢሆን ቢሆን አቶ ሀይለማርያም እስከ መጪው የ2015 ምርጫ ካልሆነም እስከ መጪው የየካቲት 2005 የኢ.ህ.አ..ዴግ ጉባኤ እንኳን የተጠባባቂ ጠቅላይ ሚንስትር መንበሩን ይረከቡ ይሆን ? ከተረከቡስ ሲጠሯቸው አቤት ሲልኳቸው ወዴት ባይ ሎሌ ይሆናሉ ? ለስንቱ ጌታስ ይታዘዙ ይሆን ? ለአዜብ ፣ለበረከት ወይስ ለአቦይ ስብሀት አክራሪ አንጃዎች ? ከደፍሩስ ከህሊናቸው ጋር ተላትመው ስልጣን በገዛ ፈቃዳቸው የሚለቁ ዳግማዊ ጊዳዳ ይሆናሉ? የህውሃት ስንጥቆችስ እንደ ቀድሞው በቦናፓርቲዝም ትንተና ተገፈታትረው ይወጣላቸው ይሆን ወይስ ደም መቃባቱ ይኖራል? መቼስ የድርጅት ሊቀመንበርንቱን ህ.ው.ሀ.ቶች ለማንም እንደማያሰነኩ ጥርጥር የለውም። በመሆኑም ከቀብር መልስ ሽኩቻው አይቀሬ ይመስላል። የነዚህ ሁሉ የመንታ መንገድ ጥያቄዎች ጋጋታ ውስጥ የከተቱን የአቶ መለስ ግለ- ባህሪያትና እነዚህን ባህሪያት ለመውረስ በሚግተረተሩ የመንደር ጓዶቻቸው ምክንያት መሆኑን ስንገነዘብ ምንኛ ሀዘን ይሰማን ይሆን? ወይ ኢትዮጵያ? !